# ካርቱም ውስጥ በእስር ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ተማጽኖ

ስደተኞቹ የታሰሩት የስደተኞች ዋስ ጠበቃ መሆን በሚገባው በስደተኞቹ መስሪያቤት ከሳሽነት በመሆኑ ህይወታቸው አደጋ ላይ ነው። ሰኞ ሚያዚያ 30 ቀን ታስረው ማክሰኞ ፍርድ ቤት በነጻ ቢለቃቸውም ለጸጥታ አስጊ ናቸው በሚል የስደተኞቹ መስሪያቤት በድጋሚ እንዳሳሰራቸው ስደተኞቹ እና ጉዳዩን የሚከታተሉ ኢትዮጵያውያን አረጋግጠዋል። አሁን በእስር ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያን 1. አብዱ እንድሪስ 2. ሰመረ አወቀ 3. ሰለሞን ተሰፋየ 4. ደስታ 5. አዱኛ 6. ፋሲል 7. መሃመድ 8. ሃይሉ ሲሆኑ  ስደተኞቹ ከማክሰኞ ግንቦት አንድ ጀምሮ እስከ ግንቦት አራት 1998 ዓ.ም ፖሊስ ጣቢያ የነበሩ ሲሆን ከአርብ ጀምሮ ሙግረን ወደሚገኘው እስር ቤት ተወስደዋል። ስደተኞቹ ፍርድ ቤት ቢቀርቡ እንደሚለቀቁ ስለሚያውቅ የስደተኞቹ መስሪያቤት የተጠናከረ ክስ ይዞ ለመቅረብ በዝግጅት ላይ ነው ሲሉ ስደተኞቹና ጉዳዩን የሚከታተሉ ያላቸውን ስጋት ይገልጻሉ።

የስደተኞቹ መስሪያቤት የጸጥታ ስጋት ናቸው ሲል በፖሊስ ያሳፈሳቸውና ያሳሰራቸው ኢትዮጵያውያኑ ለግንቦት አንድ ቀን 1998 ዓ.ም ከፍተኛ ረብሻና በመስሪያቤቱ ንብረትና ባልደረቦች ላይ አደጋ ለመጣል ማሴራቸውን መረጃ ደርሶኛል በሚል መሆኑን ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ። ስደተኞቹ ይህን የማድረግ አቅምም ሆነ ፍላጎት እንደሌላቸው በመግለጽ አሌ ይላሉ።
ከታሰሩት ውስጥ አብዱ እድሪስ የተባለው ኢትዮጵያዊ ከወር በፊት የስደተኞቹ መስሪያቤት በኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈጽመውን ግፍ አጥብቆ መቃወሙን ለመግለጽ የስደተኞቹ መስሪቤት ባለ ስልጣናት ባሉበት ሰውነቱ ላይ ቢንዚን በማርከፍከፍ ራሱን ክብሪት ለኩሶ እንደነበርና ለጥቂት አካባቢው በነበሩ ሰዎች ርብርብ ህይወቱ ተርፏል። ይህ ኢትዮጵያው ፍርድቤት ቀርቦ የደረሰበትን ግፍ በማስረዳቱ ዳኛው የስደተኞቹ መስሪያቤት ጉዳዩን በፍጥነት መፍትሄ እንዲፈልግለት አዞ በነጻ ለቆት ነበር።

የስደተኞቹ መስሪያቤት የፕሮቴክሽን ክፍል ባልደረባ የሆነው ሚስተር ዲያዲን ለምን መስሪያቤቱ እንዳሳሰራቸው ተጠይቆ ያሰራቸው የጸጥታ ስጋት በመሆናቸው ፖሊስ እንጂ የስደተኞቹ መስሪያቤት እጅ እንደሌለበት ተናግሯል። ይሁንና የአይን ምስክሮች እንደገለጹት ለወራት ይጠለሉበት የነበረውን የካርቶን ቤት ያፈረሰውና ፍርስራሹን ከነእቃቸውን ጭና የወሰደችው የስደተኞቹን መስሪያቤት አርማ ያደረገች መኪና መሆኗን መስሪያቤቱም ለሶስት ቀን አግልግሎት መስጠት አቁሞ እንደነበርና በፖሊስ ሲጠበቅ ነበር።

ታስረው እየተንገላቱ ያሉት ኢትዮጵያውያን በሁለት የሚመደቡ ስደተኞች ናቸው። የተወሰኑት ኤርትራ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚዎች ድርጅቶች  አባላት የነበሩና በስደተኞቹ መስሪያቤት የስደተኝነት መብት የተሰጣቸው ግን የሱዳን መንግስት አገር ለቀው እንዲወጡለት በመፈለጉ የስደተኛ መታወቃ የተነፈጋቸው ናቸው። እነዚህን ስደተኞች የሱዳን መንግስት ለስደተኞቹ መስሪያቤት አስፈርሞ ከ10 ወራት በፊት ያስረከበው በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ እፈልጋለሁ በማለቱ ነበር። የተቀሩት  ደግሞ ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ  ከኢትዮጵያ የተሰደዱ ናቸው። ሁሉም መኖሪያ ቤትና መታወቂያ ስለሌላቸው  የስደተኞቹ መስሪያቤት ጉዳያቸውን እንዲያይላቸው መስሪያቤቱ ደጃፍ ላይ አብረው ለአራት ወራት አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ የነበሩ ናቸው። አብሮ ታስሮ የነበረ ኤርትራዊ ስደተኛን የስደተኞቹ መስሪያቤት ሲያስፈታ ኢትዮጵያውያኑን ፋይል የላቸውም ማለቱ ጉዳዩን ይበጥ አሳሳቢ አድርጎታል።

በተለይ ከኤርትራ የመጡት የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አባላት የነበሩት ከፍተኛ ስጋት አለባቸው። ወደ ሱዳን ሲገቡ ግርባ የተባለ እስር ቤት ማሞ እንየው የተባለ ጓደኛቸው  ተነጥሎ

መቅረቱን አሁን በቅርቡ ደግሞ የስደተኞቹ መስሪያቤት በራፍ ላይ ማደር ከጀመሩ በኋላ ደረጀ ቦጋለ  የሚባል ጓደኛቸው የት እንደገባ ማወቅ ባለመቻላቸው ከፍተኛ ስጋት ላይ መሆናቸውን ይገልጻሉ። እንደ ስደተኞቹ ከሆነ ግርባ ላይ የቀረውን ማሞና አሁን ከወር በፊት ከአጠገባቸው የተሰውረው ደረጀ ህይወት አደጋ ላይ ወድቋል  የሚል ስጋት አላቸው። ይኸነው የተባለ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኛ ግንባር አመራር አባል የነበረ ኢትዮጵያዊን ወያኔ በ2002 ከሱዳን ጠልፎ መውሰዱና ከምርጫው በኋላ ባህርዳር ውስጥ ተገሎ ተጥሎ መገኘቱ የሚታወስ ነው።

ግንቦት 8 ቀን 1998 ዓ.ም ከተፈታው ኤርትራዊ ማወቅ እንደተቻለው ፖሊስ ጣቢያም ሆነ እስር ቤት ማዋከብ፤ ጡቻና እርግጫ ይደርስባቸዋል። ጠያቂ ስለሌላቸው ከፍተኛ የምግብ ችግር አለባቸው። የሙቀቱ መጠን ከአርባ ዲግሪ ሴንቲግሬድ በላይ በሆነበት ካርቱም ያለምንም ሙቀት ማቀዝቀዣ የሌለው ክፍል በመታሰራቸው ከፍተኛ ስቃይ ላይ ናቸው።

በመሆኑም የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ድርጅቶችና ግለሰቦች የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች መስሪያቤት እነዚህን ስደተኞች እንዲያስፈታ ለጉዳያቸውንም ተገቢዎን ትኩርት እንዲሰጥ በመማጸን የታሰሩትን ኢትዮጵያውያን ህይወት እንዲታደጉ ይማጸናሉ።